# <u>ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል</u>

ክፍል 2

የበሰለ ፖለቲካና ትግል ባህልና ልምድ ሲጠፋ ወይም ሲደበዝዝ አሉባልታ በየመድረኩ መንገሱ የሚጠበቅና የታየም ነው:: በተለይም ስርዓቱ በሀሰት ላይና በአጭበርባሪነት ላይ የተገነባ ከሆነ ህብረተሰቡን ይበክለዋል:: ዛሬ የማስታወቂያ ሚኒስቴር የሚባለው በአፄው ዘመን በፊት ለፊት ፕሮፓጋንዳ ሚኒስቴር ነበር የሚባለው:: ለአገዛዙ ቅስቀሳ ለማድረግ የተመሰረተ ተቋም ማለት ነው:: አሜሪካ ለምሳሌ በሀገሪቷ ውስጥ በአጭር ሞገድ የሚያስተላልፍ የመንግስት ራዲዮ ወይም ቴሌቪዠን የለም--በህግ ክልክል ነው:: መሰረቱ መንግስት በሕዝበ ላይ ፕሮፓጋንዳ ማድረግ የለበትም የሚል ነው--ይህ ይባል እንጂ አሜሪካ የውጭ ሀገር ዜጎችን በራሱ ፕሮፓጋንዳ ለመቀየስና አንጎላቸውን ለማጠብ በቢሊዮን ደረጃ ገንዝብ ያወጣል:: የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ተብሎ ወደ ኢትዮጵያ በአማርኛ፤ ኦሮሚፋና ትግሪኛ የሚያስተላልፈው ተቋም ተልዕኮው የአሜሪካንን መንግስት አቅዋምና መስመር በቀጥታም በእጅ አዙርም ማስተጋባትና ለዚህ አቅዋምም ድጋፍ መፈለግ ነው:: አሜሪካ ፕሮፓጋንዳ ያሰራጭብናል፤ ይነዛብናል ማለት ነው:: ለዚህም ነው አንዳንዶች ቀላል ሰለባ ሆነው የአሜሪካ አቅዋምና ፖለቲካ ምንኛ ኢትዮጵያንና የአፍሪካ ቀንድን በአጠቃላይ እየጎዳ እንዳለ ማየት ተስኗቸው አሜሪካ ኢትዮጵያን ከወያኔ ነፃ ያወጣልናል ብለው የሚመኙ ትናየሚሞኙት:: በደፈናው ፕሮፓጋንዳ ወይም ቅስቀሳ አሉታዊ ነው ማለት አይደለም:: ማንኛውም ድርጅት መርሀ ግብሩ ተቀባይነት እንዲያገኝ መቀስቀስና ማስተማር አለበት:: መንግስትም ወይ ስልጣንን የያዘው ቡድን መስመሩን ለማስጨበጥና ድጋፍ ለማግኘት ቅስቀሳ ማካሄዱ የሚጠበቅ ነው:: የሕዝብን ንብረት ተቆጣጥሮ ማለትም መገናኛ ብዙሃንን በራሱ ቁጥጥር ስር አስገብቶ በሕዝብ ኪሳራ ሕዝብ ላይ ቅስቀሳ ሊያካሂድ ግን መፈቀደ የለበትም:: የመንግስት ቁጥጥርመሰረዝ አለበት ማለት ነው:: ይህ በዚህ እንዳለ ወደ ቅስቀሳ ስንመለስ የቅስቀሳ ሚና አዎንታዊ የሚሆነው አሉባልታና ውሸት ላይ ሳይመሰረት ብቻ ነው:: ውሸትና ሀሰትን ማሰራጨት ቅስቀሳ ሳይሆን ማደናገርና መጥፎ መልዕክትን ማስተላለፍ ነው:: ጣሊያን ኢትዮጵያን ሊወር ሲነሳ የሀገሪቷን ገፅታ አበላሽቶ በማቅረብ ራሱን አንድ አሰልጣኝና ነፃ አውጪ ሊያስመስል ሞክሮ ነበር::ሕዝብንም ለመከፋፈል በአማራው ላይ በክርስቲያኑ ላይ ያልነዛው የሀሰት ፕሮፓጋንዳ አልነበረም:: ሰማዕት አቡነ  ጴጥሮስና በደብረ ብርሃን በገፍ የተገደሉት ካህናት፤ በአዲስ አበባ ተለቅመው የተፈጁ የዚያን ጊዜ ምሁራንም የሚረሱ አይደሉም:: የአፄው መሰረታዊ ውሸት ራሳቸውን ስዩመ መለኮት፤ስልጣኑ የማይጠየቅ የማይገረሰስ ብለው ማቅረባቸው ነው ማለት ይቻላል:: ይህን ሀሰት ያጋለጡ ሁሉ ( ባህታውያን ሳይቀሩ) ተገርፈዋል፤ ታስረዋል፤ተግዘዋል:: ሀሰት ራሱን የጠበቀውና እውነት ነኝ ብሎ ሊሰየም የቻለው በጠመንጃና በአፈና ብቻ ነበር:: ግን የካቲት 66 ደግሞ ይህን ሁሉ ውሸት መና አስቀርቶ ያን ክፉ ስርዓት ከታሪክ ትቢያ ከቶታል:: እንኳን ሰው ዝንብም አልገል ባዩ የዋሸ ዋሾ ኮለኔል ደግሞ መላ ስርዓቱን በውሸት ለስኖ ሊያቆም የቃጣና የሞከረ እንደነበር ዛሬ ያለውም ብዙሀኑ ዜጋ የሚያውቀው ነው:: ወጣቱ ትውልድ ሀሰትና ውሸት ሲጎርፍበት በተወሰነ ደረጃ እውነት መስሎት ሊያምን ቢቃጣም በመሰረቱ የመንግስቱ አገዛዝ

የቀጣፊዎችና የነፍሰ ገዳዮች አገዛዝ መሆኑን ማንም የሚስተው አይደለም፡፡ ይህም ኃጢያት በመ ሰረቱ የዚያን አገዛዝ ቁንጮዎች፤ አራጆችና ተጠቃሚዎች ይመለከታል እንጂ በጅምላ ሁሉም በዚያን ጊዜ ተቀጥሮ የሰራን ዜጋ የሚበክል እንዳልሆነም ግልፅ ነው፡፡

የወያኔ አገዛዝ ሲመሰረት ጀምሮ ማገሩም ምስሰውም ገመዱም ሳሩም ውሸት ውሸት ብቻ ነበር፡፡ የሀሰት ትረካ ፅፎ በመነሳት ኢትዮጵያን ገና ከናቅፋ ደደቢት ሲነሳ ዘርዞ ሁሉም ብሄረሰብ ይገንጠል ብሎ መርሀ ግብሩን አወጀ ፡፡ ሀሰት ውሸት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከገዢዎቹ ተቃረነ እንጂ እርስ በርስ አብሮ የማያስኖረው ቅራኔ አልነበረውም፡፡ ይህነ ሀቅ የሚናገሩትን እንደ ኢሕአ ፓ ዓይነት ህብረ ብሄር ድርጅቶችን ደግሞ የአማራ ትምክተኛ ድርጅት፤ የሸዋ አስመሳይ ተራማ ጆችእያለ በሀሰት ወነጀለ ፡፡ከትግራይ መሬት ውጡልኝ ሲልም ብረት ወድሮ ጠየቀ ፡፡ ዛሬ ኢሕአ ፓ በወያኔ ላይ ጦርነት ከፈተ ብለው ሀሰት የሚያናፍሱ የወያኔ የዛሬም የቀድሞም መሪዎች እን ደሚሉት ሳይሆን ኢሕአፓ ከወያኔ አመራር ጋር ዘጠኝ ጊዜ ተደራድሮ ትብብርን ቢሻም ዋናውና መሰረታዊ ልዩነት የነበረው ወያኔ ኢሕአፓ ከትግራይ ምድር ይውጣ ብሎ በመድረቁ ነበር፡፡ ዘር ከሉጋም እንዲሉ አንድ የትግራይ ምሁር በጠባብ ብሄርተኛነት ተሸንፎ ወያኔን የአርሶ አደሩ መንግስት ብሎ በመሰየም ኢሕአፓና ወያኔ የተጋጩት ኢሕአፓ ወያኔን በእኔ ስር ሆነህ ታገል ስላለው ነው ብሎ የዋሸውና የፃፈው ግለሰቡን ከማስገመት ባሻገር ሀቁን የሚደብቀው አል ሆነም፡፡ በግንባርም በትብብርም አሊያም በሁሉም መስመር ዓላማችን ከገጠመ በውህደትም ደረጃ እንተሳሰር ብሎ ኢሕአፓ አማራጭ ቢያቀርብም ወያኔ መጀመሪያ ከትግራይ ውጡልን፤ የትግራ ይ ሕዝብ መሪ እኛ ብቻ ነን ብሎ እምቢ ማለቱ የግጭቱ መንስዔ መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ በዚህ በወያኔ የከረረና ጠባብ አቅዋም ተባባሪ በመሆን የኤርትራ ግንባሮች--ጀብሀም ሆነ ሻዕቢያ -- በተለያየ ደረጃ ቢሆንም ተባብረዋል፡፡ የኢሕአፓን ሰራዊት /የኢሕአሠን/ ጥይት በመያዘ ጀብሀ ሲተባባር ሻዕቢያ ደግሞ የወያኔን ሀይል በሰውና በከባድ መሳሪያ በመደገፍ ኢሕአፓ ትግ ራይን ለቆ እንዲወጣ አስገድደዋል፡፡ ከዚያም ተባብረው በፖለቲካውና በዲፕሎማሲያዊው መስክ ፀረ ኢሕአፓ ትግል አካሂደው በጎረቤት ሀገሮች በተለይም በሱዳን ብዙ ችግር በድርጅቱ ላይ ፈጥረዋል፡፡ ወደ ጎንደር ዘልቆም ወያኔ ኢሕአሠን በተደጋጋሚ ወግቷል-- ወልቃይት ጠገዴና ፀለምት የትግራይ መሬት ነውና ውጡ በሚል፡፡ የደርግ ፍፃሜ ጊዜም በሀይል ደረጃ ተባብረውና በሱዳንም ተደግፈው ኢሕአሠን በጎንደርና ጎጃም መውጋታቸው ሀቅ ነው፡፡ ይህን ለመካድ የሚነዛ ወም ዳሽን ተራራን የበለጠ ውሸት እርቃኑን ወጥቷል፤ ፈርሷል፡፡

ያወቁ መስሏቸው፤ ያስጠሉ መስሏቸው፤ በሀገር ዜጋና ምሁር ላይም የሰናፍጭ ፍሬ ያህልም እምነት መያዘ አቅቷቸው ሁሉንም ፋሮሪና አሽከርካሪ ሰሜኖቹ ማለትም ኤርትራውያን ነው ብለው የሚቃዡና ሌላውንም ሊያሳምኑ የሚጥሩ ክፍሎች ደግሞ በማያውቁት ታሪክ ወንዝ በድፍረት ገብተው ኢሕአፓን ሻዕቢያ መሰረተው ሲሉ ይዋሻሉ፡፡ ለለውጥና ለሕዝብ የታገለውን የተማሪ እንቅስቃሴ ሁሉ የሻዕቢያ ፍጡርና መሳሪያ አድርገውም ለማቅረብ ሲነሱ ቅንጣትም ሀፍ ረትና አደብ አልታየባቸውም፡፡ ወያኔና ሻዕቢያ በበኩላቸው የተዛባ ታሪክን ማስተጋባት ከፖለቲካ

አቅዋማቸው ጋር የተሰፋና የተያያዘ በመሆኑ የዜጎች ትግል በዚህ መልክ በነሱ መሳሪያነት መቅ ረቡ ያስደስታቸዋል። ከእኛ በላይ አዋቂ፣ ከእኛ በላይ ተዋጊ፣ ከእኛ በላይ ስልጡን የለም ብለው ይውገረገሩ የነበረውን ያጠናክርላቸዋል። ሌላውን ሁሉ ተስፋ ያስቆርጣል፣ የዝቅተኛነት ስሜት ያስይዛልና ይህ ሀሰት መሰራጫቱን ይፈልጋሉ፣ ይወዳሉ። በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበሩ የሰሜን ተወላጆች በኢትዮጵያዊነታቸው አምነው የታገሉና አልፎም ህይወታቸ ውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጡ ናቸው። ወደ ግንባሮቹ ሄደው የጠበበውን እናሰፋለን፣ አቅጣጫ እናስይዛለን ወዘተ ብለው የሞከሩ ደግሞ በህይወታቸው ለስህተታቸው ከፍለዋል፣ ተገድለዋል። የተማሪውን ትግል ሆነ ኢሕአፓን ወደ ሻዕቢያና ባዕድ ሊያቆራኙ የሚጥሩት ደግሞ ሀገር በቀል ችግሮች መኖራቸውን ለመካድ ነው። በአፄው ዘመን የስርዓቱ ግፍ ሕዝብን ለአመፅና ለትግል እ.ንደገፋፋውና ተማሪውም ሆነ ኢሕአፓ ወይም ጭቁኑ ሕዝብ መፈክሬ ያላቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች (መሬት ለአራሹ፣ ዴሞክራሲ ለሕዝብ፣ ድህው ይማር፣ እኩልነት ይከበር ወዘተ...) መንስዔያቸው የነበረው ኢፍተሃዊና ፀር ዴሞክራሲ ስርዓት ነው። አንድም ሆነ ግማሽ ጥያቄ ከአየርና ከገዋ አልተቦጨቀም። የነበሩ ችግሮች ለተከሰቱ መፈክሮች እናቶች ሆኑ እንጂ። በመሆ ኑም ኢሕአፓ ወይም የተማሪዎች እንቅስቃሴ ብሄረሰቦች አይጨቆኑ ስላለ ብሄረሰቦች ተነስተው አላመፁም--ያመፁት ገና እንቅስቃሴው ሆነ ኢሕአፓ ሳይመሰረቱ ወይም ይህ ነው የተባለ የለው ጥን ትግል ገና ሳይጀምሩ ነውና። የተማሪው ትግል ያነገባቸው መፈክሮች ሕዝባዊ ነበሩ--መሬት ለአራሹ ዋነኛው ነው። የፊውዳል ልጆችና ተጠቃሚዎች፣ ከገባሩና ጪሰኛው ላብ ብር አምራቾ ች በዚህ መፈክር ቢበሳጩ የሚጠበቅ ነው። ግን ኢሕአፓ በባዕድ ተመስርቶ፣ የባዕድ ርዕዮት ተከ ትሎ የሌለ ችግርን ቀፈቀፈ ብሎ መዋሸት አሳፋሪና ዋሾዎቹንም የሚያጋልጥ ነው። በየካቲት አብዮት ሕዝብ በብሄረሰብና በሀይማኖት ሳይከፋፈል ታገለ ፣ ኢትዮጵያውያን እስላሞች ባካሄዱ ት ሰልፍ ክርስቲያኑም ደግፎ ተሰለፈ ፣ሴቶች ለመብታቸው ታገሉ እንጂ ሕዝብ አልተከፋፈለም። የየካቲትም ሆነ የኢሕአፓ ትግል መልዕክት የክፍፍል ሳይሆን የአንድነት፣ ለባዕድ መገዛት ሳይ ሆን ሉዓላዊነት፣ አምባገነንነት ሳይሆን ዴሞክራሲያዊነት ነበር/ነው። ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስቃይ ባቃጠላቸው ሀገር ወዳድ ልጆቹ የተመሰረተ፣ ህብረ ብሄርና የሕዝብ ድርጅት ነው።የኤርት ራ ችግር ከኢሕአፓ ምስረታ በፊት የነበረና የተባባሰ ሆኖ ሳለ ኢሕአፓ ችግሩ በሰላማዊና ዴሞክ ራሲያዊ መንገድ ይፈታ፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ይከበር በሚሉ አቅዋሞች ዙሪያ ቢንቀሳቀስም አቅዋሙንና የግንባሮቹን የጠባብ ብሄርተኛነትን አደጋ ከመረመረ በኃላ በወሰደው ይፋ አቅዋም ችግሩ በፌዴሬሽን ምስረታ መፈታት አለበት ብሎ አቅዋሙን በዴሞክራሲያ በማስ ፈሩ የሻዕቢያንም የወያኔንም ውርጅብኝ ተቀብሏል። ወያኔና (የዛሬው ቁንጮው) ኤርትራ ቅኝ ግዛት ናት ብለው መፅሀፍ ሲፅፉና ከኢትዮጵያ መለየቷም የግድ ነው ብለው ሲቧርቁ ኢሕአፓ ይህን አቅዋም በመፃረርና የወታደራዊውንም ቡድን የከሰረ ፖለቲካ በማውገዝ ችግሩ በፌዴሬሽን ምስረታ ይፈታ የሚል አቅዋምን አቅርቧል። ሀቁ ይህ ነው። ኢሕአፓ ለኤርትራ ግንባሮች ያኔም ቢሆን ዛሬ መሳሪያ አልነበረም/አልሆነም--ታዛዡነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ጥቅም ብቻ ነውና። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ስንት ሚሊዮን ተወላጅ ያለውን ብሄረሰብ (ለምሳሌ ኦሮሞና አማራ) በጎሳ ደረጃ ለመሰየም መነሳትና ብሄረሰብ የሚለው ቃልም ይሰረዝ ማለት ከሳይንስም ከተጨባጩም

ሁኔታ የሚያጣላና ይፈለጋል የሚባለውንም አንድነት የሚያርቅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ህብረ ብሄር ሀገር መሆኗ፣ ዜጎቿ የልዩ ልዩ ሀይማኖት ወይም እምነት ተከታይ መሆናቸው መርገሚ ወይ ሽክ ሚ ሳይሆን ጌጧና ፀጋዋ መሆኑን መቀበል የግድ ያስፈልጋል፡፡ የሀገርን አንድነት በጉልበት ወይ ም የጭቆናን ዘመን መልሶ ከነግሳንግሱ በመትከል ለማስጠበቅ መጣር ወይም መመኘት ሀገራችን ን ይጎዳል፡፡ የኢሕአፓ አቅዋምና ሀቁ ይህ ነው፡፡ ታዲያ ምን ያስዋሻል?

የነበሩት ስርዓቶችና አገዛዞች በሞላ የሀገሪቷን ዋና ዋና ችግሮቹ እንኳን ሊፈቱ ያባባሱ ናቸው፡፡ ኢሕአፓ የነሱን ቆሻሻ ሊያፀዳ ጣረ እንጂ ንፁሁን ቤት በአቧራ አልሞላውም፡፡ ያበጠው ይፈንዳ ያለው ትውልድ ጥቂቶች በብዙሀኑ ላይ ሽክም መሆናቸው ያብቃ ባይ ነበርናም በጥገና ለውጥ ወይም ዛሬ እንደሚባለው በመጪው ምርጫ እስቲ እንሞክራለን በሚል ባዶ ተስፋ ሕዝብን መሸንገል የመረጠ አልነበረም፡፡ የደላውና የከበረ ተቃዋሚ አልነበረም፡፡ የሕዝብን መከራ በቅርብ የሚያውቅ፣ ኑሮው ሻል አለ ቢባልም ከዝቅተኛ ደረጃ ከፍ ያላለ ና በኔ ብጤነት ከብዙሃኑ የሚጠ ቃለል ነበር፡፡ በእርግጥም አገዛዙ ሊደልለውና አዋቂና ምሁር ነህ ብሎ ከሕዝብ ሊነጥለው ቢሞክ ርም ያ አኩሪ ትወልድ ያሰተማረውን ሰፊ ሕዝብ ሳይረሳ ሀገር ለሁላችንም አሊያም ለጥቂቶች ከበርቴዎችና በዝባዦች አትሆንም ብሎ ዱሩ ነው ቤቴ በሚል አምጿል፣ በቀይ ደም የተከተበ ታሪክንም ፅፏል፡፡ አፄው የተማሪውን እንቅስቃሴ በባዕዳን የሚመራ (በጊዜው በሶቭየተ ኅብረት ለማለት ነበር) ነው ብለው ሀሰት ሲያሰራጩ ደርግ ደግሞ ኢሕአፓን ከአረብና ከአሜሪካን ሲ አይ ኤ አቀራኝቶ ና ኋላም ከዚያድ ባሬ ሶማሊያ ጋር አስተሳስሮ በማቅረብ ከሕዝብ ሊነጥል ሞክሯል፡፡ ዛሬ ወያኔ በተቃዋሚ ሀይሎች ላይ የሚነዛው የሀሰት ክስና ዘመቻ ሌላ ምስክር ነው፡፡ በዚህም መሰረት የትላንት ወንጀለኞች የዛሬ ታሪክ ዘጋቢዎች ሆነው የኢሕአፓን ስም እንዲያጠ ፉ ድጋፍና ትብብር እየሰጠ ነው፡፡ መድረኩም በነዚሁ ከርፍቶ ባለበት የይሉኝታ ልጓም በመበጠ ሱ አሰቃቂ ወንጀሎችን--ቀይ ሽብርን ሳይቀር- በገሀድ እስከመካድ ደርሰዋል፡፡ ካጂውም አራጋቢ ውም ትላንት የዚያ አረመኔ ስርዓት ሎሌዎችና መሪዎች እንደነበሩ ግን ታሪክ የመዘገበው ሀቅ በመሆኑ ውሸት መለፈፉ ከንቱ ልፋት ነው፡፡ የትላንት ወንጀለኞቹ በንስሐ ሳያልፉ የዛሬ የሕዝብ መሪዎች ተብለው መገኘታቸውም ነገር ዓለሙን አደባላልቆታል፡፡ እውነቱ ተነግሮ ባላለቀበት ሀገር መዋሸት የግድ ሆኖ መገኘቱ መቸም ሁሌም ያስገርማል፡፡ ለሽብሩ ዋናውና ብቸኛው ተጠያ ቂ የጊዜው አረመኔ ስርዓት ሆኖ ሳለ አገዛዙን የሩቅ ተመልካች አድርገው እያቀረቡ ምሁሮቹ አልቻቻል ብለው ተፋጁ ብለው የሚከሱት ደግሞ የያኔው ሁኔታ እንኳን ሳይመጣባቸው፣ ከያኔ ከሚከሱት ተመክሮ መማር ሲገባቸው እርስ በርስ ሲናከሱና ወያኔ ደስ ይበለው በሚልም በስተር ጅና በአደባባይ ሊቧቀሱ ሲነሱም ታዝበናል፡፡ ገበያው በዚህ መልክ ሲደራም ሐራሬ የተወሸቀው ነፍሰ ገዳይም በሽብሩ እኛም አልነበረንበትም ብሎ እየለፈፈ፣ እየፃፈና እያፃፈ እንዳለ የምናወቀ ው ነው፡፡ ሁሉም አንድ ናቸው ውሸት እየተስተጋባ በደርግና በሌሎች፣ በኢሕአፓና በመኢሶን መሀል ያለው መሰረታዊና ወሳኝ ልዩነት ሊጨበጥ ካልተቻለ የዚያን ጊዜ ሀቅ መረዳት የሚቻል አይሆንም፡፡ ዛሬ ወያኔን ወዳጅ ብሎ አብሮ ሊሰራ የተነሳ ቡድንና ወያኔን ጠላት ብሎ በሁለገብ

ትግል ሊያወድም የተነሳ ሀይል በአንድ ሊሰለፉ እንደማይችሉትና እንደማይገባ ሁሉ የያኔውም ሁኔታ ተመሳሳይ ነበር። ያልተመራመሩ አይናገሩ እንደተባለው በቅድሚያ የሀገርን ታሪክና ሀቁን ለማወቅ መጣር ያስፈልጋል እንጂ ለውሸት ነፍስ ለመዝራት መዋደቁ ትክክል አይሆንም። ለዚያ ውስ እስከመቼ ሊዋሽ ነው? ማንንስ እስከመቼ ለማታለል ነው?

ኢሕአፓ ጦርነትን ሆነ ንትርክን ፈላጊ አይደለም። ፈሊጥ መስሏቸው ውሸት እየተቀባበሉ ድርጅ ቱን በጠብ ጫሪነትና ተናዳፊነት የሚከሱ አሉ። ባለፈው አገዛዝ ጊዜ ሽብርና ግድያ በደርጉ በራ ሱ ተጀምሮ ባለበት ኢሕአፓ ተኩስ ጀማሪ ነበር ብለው የሀሰት ክስ ይደረድራሉ።ይደጋግማሉ። ወያኔም በ1983 ኢሕአፓን ራሱ ወግቶ ሳለ ድርጅቱን በጦረኝነት ከሶ በሽግገሩ ጉባዔም እንዳይሳ ተፍ ለማገድ ይህንኑ ምክንያቱን ደርድሯል። ዛሬም ቢሆን ኢሕአፓን ህገወጥ ብሎና የተያዙ አባ ሎቹን ደብዛ አጥፍቶ፣በፀጥታ መስሪያ ቤት ልዩ ፀረ ኢሕአፓ መምሪያ መስርቶ በመንቀሳቀስ ላይ እያለ ኢሕአፓን በፀረ ሰላምነት ለመክሰስ ሲነሳ ምላሱንም ያዝ አድርጎት አያውቅም። ኢሕአፓ በደርግ መጀመሪያ ዘመን ባወጣው ፕሮግራም በህጋዊነትና በሰላም ለመታገል ያለውን ፍላጎት--ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከተከበሩ-- ግልፅ አድርጎ ነበር። የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ምስረታ ጥሪ ሁሉን አቀፍ ነበር። ወታደረዊው አገዛዝ የህብረት ግንባር ጥሪ ብጤ ሲያወጣም ኢሕአፓ በጭፍን የእምቢታ መልስ ሳያቀርብ ሁሉን አቀፍ እንዲሆንና በምን ምን ሁኔታም ሊመሰረት እንደሚችል ጠቃሚ ጥቆማዎችን በይፋ አቅርቦ ነበር። አገዛዙ ግን በፖለቲካው መሰክ ሽንፈቱን መቀበል ስለተሳነው በኢሕአፓ ላይ የግድያ ዘመቻ ከፈተ፣ መስከረም 2 በይፋ ጦረነት አወጀ ፣ ወደ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብርም ተሸጋገረ። ሕዝብ ሁሉ የሚያውቀው ሀቅ ይህ ነው። የወያኔን ጦርነት ጫሪነትና አረመኔነት በሚመለከት ደግሞ ብዙ ሀቍታ አቅርቡ የሚለን ዛሬ ሊኖር አይች ልም። ወያኔ ሁሉን ቻይ ና ዴሞክራሲያዊ ነው የሚሉ፣ ሰላም ፈላጊ ነው የሚሉ ወያኔዎችና ጥቂት ሆዳቸው ህሊናቸውን የገደለባቸወና ዓይናቸውን ያጠፋባቸው ግለሰቦች ብቻ ናቸው። ሆድ ሲቀድም መታወር መደንቆር ይመጣል ተብሎ የለ ? ከዚህ ሌላ ግን ኢሕአፓ ከትንሽ ትልቁም ድርጅት በሀገር ወዳድነት መለስተኛ መርህ ግብር ወይም ፕሮግራም ሲተባበር መቆየቱ የተመዘገ በ ነውና ህብረት አይፈልግም የሚለው ክስ የጠራራ ፀሐይ አሳፋሪ ውሸት ነው። በአፄው ዘመን ከኢብነአግ ተብሎ ከሚጠራው ድርጅት ጋር፣ ከአፋሮች ድርጅት ጋር፣ ወዘተ ሊተባበር ሞክሮ ነበር። በደርግ ጊዜም ከኢዲኅና ሌሎችም ጋር ህብረት መስርቶ ነበር። ደርግ ሊወድቅ አካባቢ ደግሞ ከኢዲኅ፣ መኢሶንና ሌሎችም ጋር ሆኖ አዴኃቅን መስርቶ ነበር። ከዚያም ለፓሪስ ጉባዔ፣ ለኢተፖድህ ምስረታ፣ ለግዮኑ የሰላምና ዕርቅ ጉባዔ፣ ከዚያም ለኢዴኃኅ ምስረታ ኢሕአፓ ግንባ ር ቀደም አካል ሆኖ ተንቀሳቅሷል። በእኩልነት፣ በጋራ ፕሮግራም። ለምሳሌ የኢዴኃኅ መሰረታ ዊ ሰነዶች የተረቀቁት በሀገር ቤት ህጋዊ ሆነው በሚሰሩ ድርጅቶች ከመሆኑ ሌላ ዋና ዋና የአመራር ቦታዎችም የተሰጡት ለነሱው ነበር። ኢሕአፓ ይህ ድርጅት ገደሎኛል፣ አድምቶኛል፣ ትንሽ ነው፣ ሰው የለውም ሳይል በእኩልነትና በአንድ ድምፅ ባለቤትነት የታገለ መሆኑ መቸም ሊካድ የማይገባው ሀቅ ነው። ከዚህ ባሻገር ግን ድርጀቶች የተሳሳተ መስመር ሲገፉ ወይም ሕዝብ ን ሲክዱ ኢሕአፓ ተችቷቸዋል። የፖለቲካ መስመር ትግልና የሀሳብ ልዩነትን በሰላማዊ መንገ

ድ መያዙና  በዚሁ ላይም ትግል ማካሄዱ ተናዳፊነት ሳይሆን የትግል ግዴታ ነው፡፡ ግርግር ያመቻል ብለው የሕዝብን ትግል መጠቀሚያ ለማድረግ የተነሰቱን ኢሕአፓ አጋልጧል--ይኮራል እንጂ በዚህ ስራው አያፍርም፡፡ ትላንት ከመንግስቱም ሆነ ከመለስ ጋር ሆነው ሕዝብ ላይ ወንጀል የፈፀሙ ወይም የወንጀል ተባባሪ የሆኑት አጠፉን ሳይሉ፤ ይቅርታ ሕዝብን ሳይጠይቁ ከሕዝብ ጎራ መቀላቀል ብቻም አይደል መሪ ነን ብለው ሲሞሽሩ ኢሕአፓ ተቃውሟል--ወደፊትም በተቃውሞው ይቀጥላል፡፡ ቀይ ሽብርን ሲክዱ አጋልጧል--ወደፊትም ያጋልጣቸዋል፡፡ ሕዝብን ከድተው የወያኔ መሳሪያ ሲሆኑ አውግዟል--ወደፊትም ይቀጥልበታል፡፡ የድርጅት መሪዎች የሕዝብ አገልጋይ መሆን አለባቸው የተባለውን መርህ ጥሰው ጣዖት ለራሳቸው ሲያስጠርቡ ኢሕአፓ በቃላት ወርፏቸዋል--ወደፊትም ይቀጥልበታል፡፡ ከዚህ ሌላ ግን ኢሕአፓ ማንንም አይሰደብም--ስድብና ሰው አዋራጅ ስርዓቶችን የሚታገል ስነ ስርዓት ያለው ድርጅት ነውና፡፡ ግና የፖለቲካ ትችት ስድብ የሚመስላቸውና የፖለቲካ መሪያቸው ከተተቸ የሙት ሞት የሚመስላቸው ክፍሎች ምናልባትም ስህተታቸውን ለማረምና ንቃታቸውን ለማሳደግ መጣር ይገባቸዋል እንጂ በኢሕአፓ ላይ የሀሰት ክሶችን መደርደር አይጠቅማቸውም፡፡ የሕዝብ ትግልና የሀገር ህልውና ጉዳይ ስለሆነም ከዚህ በፊትና በላይ ማንንም ማስቀደም ስለማይቻል የተሳሳተን ተሳሳተ፤ የከዳን ከዳ ማለቱ ለኢሕአፓ ግዳጄ ከሚላቸው አንዱ ነው፡፡ በዚህም ረገድ ለምሳሌ ገና ከእንጭጩ ክህደቱ የነበረውን ግለሰብ ማጋለጡና የሕዝብን ጎራ ተጠንቀቁት ማለቱ የሚታወስ ቀና ስራ ነው፡፡ ክህደት ስንፈፅም፤ ቃል ኪዳን ስናፈርስ፤ ለወያኔ  የሚጠቅም ስራ ስንሰራ፤ የሕዝብን ጎራ ስናተራምስ፤ ከድርጅት ድርጅት እየዞርን ስንበጠብጥ፤  ወንጀላችንን ስንክድ ዝም በሉን ቁጣ ኢሕአፓ አይቀበልም፡፡ ስለማይቀበል ግን በሀሰት ሂሶች   ብዕሩን ለማዶልዶም መጣሩ ውጤት አልባ ነው፤ ይሆናልም፡፡ ለውሸት የለው ፍሬ ነው በመጨረሻው፡፡

ይቀጥላል